# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የስትራቲጂያዊ ጉዳዩች ኢንስቲትዩት

# የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የስትራቴጂያዊ ጉዳዩች  ኢንስቲትዩት

## የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት የተመደበለትን መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2013 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲተዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን  የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኢንስቲትዩቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ  ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት

- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

**<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>**

**የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣**

**<u>የወጪ ሂሳብ፤</u>**

1. ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሐ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣውና መመሪያ መሰረት እሰከ ብር 200,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች እንዲሁም እስከ ብር 150,000.00 የአገልግሎት ግዥ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ እንዲፈፀም ያዛል። ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ ሂሳብ ለማዘጋት በሚል የኢፍሚስ ሙያ ያለው ባለሞያ እንዲያግዘን በማለት ያለምንም ውድድር እና መስፈርት ሰራተኛ በመቅጠር ብር 56,200.00 አለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። በዚህም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል።
2. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል2 ተራ ቁጥር 10 የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ አከፋፈል ፤የመንግስት ሰራተኞችን ደሞዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት ሊወስዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ ተ/ቁ 1 የስራ መደቡ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ያለው መሆን እንዳለበት ይገልጻል። ይሁን እንጅ ለኢንስቲትዮቱ ሠራተኞች የመንግስት ተሻሚዎችን ሳይጨምር ከሀምሌ 1/2012 እስከ ህዳር 30/2013 የከፈለው ደመወዝ ብር 652,118.93 የደመወዝ እስኬሉና የስራ መደቡ ባለመታወቁ እንዲሁም የተለያዩ የአበል አይነቶች / የቤት አበል የትራንስፖርት አበል የልጅ ት/ቤት አበል../ የተፈቀደበት ማስረጃ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 290,660.67 በድምሩ ብር 942,779.60 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ የደመወዝና የአበል ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።
3. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል2 ተራ ቁጥር 10 መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ አከፋፈል የመንግስት ሰራተኞችን ደሞዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት በመንግስት የሚሾሙና በዝውውር ለሚመደቡ

ሰራተኞች ይህንን አስመልክቶ የተሰጠ ትዕዛዝ መኖር እንዳለበት ይገልጻል። በመሆኑም በሚመለከተው አካል ለቦታው የተፈቀደ ክፍያ መሆኑን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 53,760.00 አለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። በዚህም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ ብሏል ።

4. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሠረት የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ (በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር) በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ እንደሚሆን በተመለከተው መሰረት የቀድሞው የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ/30/ጠ/13/36/8/3 ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ መመሪያ ያወጣ ቢሆንም ጳጉሜ 5 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ/30/ጠ/13/37/820 በጻፈው ደብዳቤ መመሪያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ በደብዳቤ ተገልጿል። በተጨማሪም ከመደበኛ ወጪ የትርፍ ሰአት ክፍያን በተመለከተ በመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስራ ላይ የሚውለው በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ሲፈቅድ ብቻ መሆኑን ይገልጻል:: ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ የሚመለከተውን መ/ቤት ሳያስፈቅድ አላግባብ በድምሩ ብር 20,257.01 የትርፍ ሰዓት በሚል ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል። በዚህም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል ።

5. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቀን 24/12/05 በደብዳቤ ቁጥር ሲ.ሰ.ማ/ሚዴን/127/05 የተሿሚዎች የቀን ዉሎ አበል አፈፃፀም መመሪያ መሰረት እንዲሁም የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 2 አንቀጽ 5 የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል መሰረት መፈጸሙ ሲጣራ በድምሩ ብር 55,235.00 ያለአግባብ የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡የወጪ ሂሳብ ሪፖርቱ ከፍ በሎ እንዲታይ አድርጎታል።

6. የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 3 አንቀጽ 9 የቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅጾች ከቁጥር 1-4 ከመደበኛ የስራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ ስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፤ መክፈያነና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሰራተኛ እንዲሞሉ ያዛል ። ይሁን እንጂ በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመሰከሪያዎች መነሻና መመለሻ ቀን፤ ሰዓት፤ ቅጽ 1፤ የሚሄዱበት

የስራ መዘርዝር ባለመሟላቱ ለአበል የተከፈለ ብር 67,268.80 የወጪን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

## ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የሚቀይረው ባይሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

7. በ2010 በወጣው የወጪ ቅነሳ መመሪያ ተራ ቁጥር 7 ላይ የመስተንግዶ ወጪን በተመለከተ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በድምሩ ብር 1,218,195.13 ከ ወጪ ቅነሳ መመሪያ ውጪ ለመስተንግዶ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
8. የፌዴራል መንግሥት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የሰራተኛና እና የኃላፊ ወንበሮች በብር 6,459,393.60 አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ ለተፈፀመ ግዥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
9. ህዳር 1999 የወጣው የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነፃ ህክምና መመሪያ ቁ.5 መሰረት የአገር ውስጥና የወጭ አገር ህክምን እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የመንግስት ሀላፊዎች ከደመወዛቸው 2 % እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ሀላፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል አለባቸው ይላል ፡፡ ይሁን እንጅ በኢንስቲትዩቱ በመመሪያው መሰረት ብር 3,889.03 ተቀናሽ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

10. የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 6/1 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኘው የመንግስት ሃብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ለተመራማሪዎች ጥቅማጥቅም በሚል ከታህሳስ 1/2013 እስከ ሰኔ 30/2013 በድምሩ ብር **1,152,466.00** ያለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡
11. የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በሾፌር የስራ መደብ ላይ ተመድበው ለሚሠሩ ሠራተኞች ልዩ አበል ስለመፍቀድ ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም በፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ/13/46/1010 በተጻፈ ደብዳቤ ከጥር 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከክፍያው ላይ ግብር እንዲቀነስ ሆኖ በመንግስት ለተሾሙ የበላይ ሃላፊዎች በዘላቂነት አገልግሎት የሚሰጡ ሾፌሮች በወር ብር 800.00 ለከፍተኛ አመራሮች ቤተሰቦች፤ ለስራ ኃላፊዎችና በመደበኛነት የሰርቪስ አገልግሎት ለሚሰጡ የሰርቪስ ሾፌሮች በወር ብር 600.00 እንዲከፈላቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ከመመሪያ ዉጭ የሰርቪስ አገልግሎት ለሰጡ ሾፌሮች የእራት አና የቁርስ አበል በሚል በድምሩ ብር **9,229.30** አላግባብ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
12. የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በተለያየ ቀንና የኢንቮይስ ቁጥር በድምሩ ብር 30,077.00 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

**<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

13. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኂላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 157,687.48 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

**ተከፋይ ሂሳብ፤**

14. በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር5/2003 ክፍል አንድ ላይ ተከፋይ ሂሳብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ሂሳብ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 679,868.23 በወቅቱ ለባለ መብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

**በጀት፤**

15. ለኢንስቲትዩቱ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ 20,037,143.45 39.13% ስራ ላይ ያልዋለ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

**ንብረት፤**

የኢንስቲትዩቱ የንብረት አጠባበቅ እና አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አያያዝ መመሪያ መሠረት መሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤-

- አስቸኳይ በሚል በቀጥታ ግዥ ከተገዙት የሰራተኛ ወንበሮች ውስጥ 31 በንብረት ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው፤
- በንብረት ክፍል (እስቶር) ውስጥ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተዉ ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው ያልተጠበቁ መሆኑ፤
  የሚወገዱ ፤ወንበሮች፤ጠረጴዛዎች የተለያዩ ዕቃዎች መወገድ ሲኖርባቸዉ ያልተወገዱ በንብረት ክፍልና ከንብረት ክፍል ወጭ የተከማቹ ሆነው ተገኝቷል፡፡

ከሰላምታ ጋር

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

## የስትራቴጂያዊ ጉዳዩች ኢንስቲትዩት

## የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት የስራ አመራር ሪፖርት

### መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የስትራቴጂያዊ ጉዳዩች ኢንስቲትዩትን የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የኢንስቲትዩቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

### የሪፓርቱ ዓላማ

የዚህ ሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለማስቻል ነው፡፡

### የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፣

- በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎች የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎች መመዘን፣
- የኢንስቲትዩቱ ሂሣብ አያያዝ የፌደራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ የተከተለ መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሠራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ በመሆኑ የሂሣብ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሣይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሣብ ሪፖርቶችን ኦዲት ማድረግና ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ነው፡፡

## የስትራቴጂያዊ ጉዳዩች ኢንስቲትዩት

## የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት የስራ አመራር ሪፖርት

የኢንስቲትዩቱ የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1 የወጪ ሂሳብ፤

### 1.1 ግኝት፤ ያለአግባብ ለመስተንግዶ ወጪ የሆነ ብር 1,218,195.13፤

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመ/ቤታቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና የፀደቀውን በጀት መሠረት በማድረግ ወጪዎችን በመፈፀም በኩል መ/ቤታቸውን የመምራት እና የመወከል፤ ፕሮግራሞችና መ/ቤታቸውን የሚመለከቱ ህጎችን በማስፈፀም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው፤ በተጨማሪም በ2010 በወጣው የወጪ ቅነሳ መመሪያ ተራ ቁጥር 7 ላይ የመስተንግዶ ወጪን በተመለከተ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ ያስፈልጋል ከዚህ ጋር ተያይዞ በየ መ/ቤቱ ለሚደረጉ ስብሰባዎች፤ወርክ ሾፖች እና ሴሚናሮች እንደ ሻይ፤ቡና እና ውሃ ከመሳሰሉት ወጪዎች በስተቀር ሌላ ግብዣ ማድረግ አይቻልም ፡፡በተቻለ መጠን ስብሰባዎች በየተቋማቱ መሰብሰቢያ አዳራሾች በማካሄድ ለሆቴሎች የሚወጣው ወጪ ማስቀረት እንደሚቻልና በቀን 18/12/2011 የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባስተላለፈው ሰርኩላር የወጪ ቅነሳው የአፈጻጸም አቅጣጫ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ

- ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮችና ቀናት ከቻይና ሬስቶራንት እንዲሁም በቀን 03/06/13 ከሂልተን ሆቴል ያለምንም ውድድር የተጋበዥ ሰዎች ዝርዝር ሳይጠቀስ እና በበላይ ኃላፊ ሳይፈቀድ ለፈታኞች ለእራት፣ለምሳ እና ሪፍሬሽመንት በሚል ብር 109,242.13 ያለአግባብ ወጪ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በተለያዩ ቀናት ከአዲስ አበባ ውጭ ከሰራተኞቹ ጋር ስልጠናዎችንና ስብሰባ በማካሄዱ አላግባብ ብር 1,108,953.00 ከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በድምሩ ብር 1,218,195.13 ከወጪ ቅነሳ መመሪያ ውጪ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**ስጋት፤**

- የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የተለያዩ ስብሰባዎች፣ስልጠናዎች፣ግምገማዎች እና ሌሎች ክንውኖች ቢቻል በኢንስቲትዩቱ በሚገኝ አዳራሽ ካልሆነም አነስተኛ ወጪ ሊያስወጡ በሚችሉ ድርጅቶች እንዲሸፈን በማድረግ የመንግስትን ውስን ሃብት መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

**የሥራ አመራሩምላሽ፤**

ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስትቲዩት በደንብ ቁጥር 374/2012 በአዲስ ተቋቁሞ አዲስ አደረጃጀት ተሰርቶለት ወደ ሥራ ከመግባቱ ከነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም በፊት ይጠራበት በነበረው የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ከ28 ያልበለጡ ባለሙያዎች የነበሩት ሲሆን በአዲስ በተዋቀረው አደረጃጀት ከ184 ሰው በላይ የሚያስፈልግና የተሟላ የምርምር ተቋም እንዲሆን በተጠናው ጥናት መሰረት ከፍተኛ የትምህር ዝግጅት ያላቸውን 33 በላይ ተመራማሪዎችን እንዲሁም ከ70 በላይ የደጋፊ የሥራ መደቦችን ቅጥር ለመፈጸም በተከናወነው የቅጥር ሂደት ኮሚቴ ተዋቅሮ የሰራተኛ ቅጥር ሲፈጸም ለቅጥር ኮሚቴዎች፣ ተመራማሪዎችን ለሚፈትኑ ከውጭ ለተጋበዙ እንግዶች እንዲሁም ለመ/ቤቱ ከፍተኛ አመራር የተጠቀሙበት ከተቋሙ ህንጻ በሚገኘው ሬስቶራንት ለምሳ አገልግሎት ሲሆን ተፈታኞች የጽሁፍ ጥያቄዎችና ከጠዋት ከተፈተኑ በኂላ ኮሚቴዎችም ለምሳ በግል ወጥተው ከሚመለሱ ይልቅ ሳይነጣጠሉ በጋራ ሆነው ምሳ በልተው ቀጣይ ለሚከናወነው የቃል ፈተናና የቅጥር ሂደቱን ታዓማኒነትና ፍታዊ የሆነ አሰራርን ይፈጥራል በሚልና እሳቤና ስራዎችን በቅልጥፍና ለመስራት የተሻለ ይሆናል ተብሎ ከበላይ ኃላፊው ፈቃድ አግኝቶ የተፈጸመ የምሳ አገልግሎት ወጪ ነው፡፡

ሌላው በተቋሙ የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ሲገመገሙና ቫሊዴት ሲደረጉ ተቋሙ የራሱ አዳራሽ ስለሌለው የሚጠቀመው በትብብር የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አዳራሽ ሲሆን የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አዳራሽ ሲያዝ አልፎ አልፎ የሆቴል አዳራሽ በኪራይ የምንጠቀም ሲሆን ለተሳታፊ እንግዶችና ባለሙያዎች የተሰጠ የምሳ አገልግሎት ነው፡፡

በተጨማሪም በስካይ ላይት ሆቴል የተደረገው ስብሰባ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ የሚመክር አስቸኳይ የክልልና የፌደራል ከፍተኛ የመንግስት ባላስልጣንና የጸጥታ ሃይሎች የሚሳተፉበት ስለነበረና ጫረታ አውጥቶ ሆቴሎችን ለማወዳደር ሁኔታው የማይፈቅድ ስለነበረና ለተሰብሳቢዎች አመች ነው ወደ ተባለው ስካይ ላይት ሆቴል ስብሰባው ተከሂዶ ምሳ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት አማካይነት ከአዲስ አበባ ውጪ ለተሰጠው ስልጠና ወጪ 1,108,953.00 አላግባብ ነው የተባለውን መተመለከተ፤</u>

ኢንስቲታችን በቂ ሰው ሃይል ቅጥር ከፈጸመ በኂላ በፍጥነት ወደ መደበኛ የምርምር ስራዎች ለመግባት ባለሙያዎች በ 3 ዙር በደብረ ዘይት ከተማ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ቅጥር ግቢ ውስጥ የስራ ማስጀመርያና የሙያ ክፍተትን በሚሞሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ ስልጠና እንዲሰጡ አድርጓል፡፡

ስልጠና ቦታው አዲስ አበባ ከተማ ለማድረግ ያልተቻለበት ምክንያት ምንም እንኳን በዋጋ ደረጃ የተወሰነ ቅናሽ ቢኖረውም ነገር ግን የተሟላ የአኮሞዴሽንና የመኝታ አገልግሎት ስለሌለውና ከስልጠና ሰዓት ውጪም ሰልጣኞች በጋራ ሆነው የሚሰበሰቡበት የሚወያበት አዳራሽ በቂ ስላልሆነና ሰልጣኙ ጊዜውን በሙሉ ለሥልጠናው በማዋል ውጤታማነቱ አዲስ አበባ ከሚሰጥ ይልቅ በደ/ዘይት ከተማ ያለው የማሰልጠኛ ተቋም የተሸለ ስልጠና ቦታ ቢሆን ውጤታማ ይሆናል ተብሎ በጥናት የተከናወነ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

<u>**የኦዲተር አስተያየት**</u>

መመሪያው በሚያዘው መሰረት የኢንስቲትዩቱ የመስተንግዶ ወጪ በመቀነስ የተፈቀደለትን በጀት በተገቢው መንገድ በመጠቀም በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

## 1.2 <u>ግኝት፤ያለውድድር በተፈጸመ የኮንትራት ቅጥር ለአገልግሎት ግዥ የተከፈለ ብር 56,200.00</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 6/1 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኘው የመንግስት ሃብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው ይላል፡፡ በተጨማሪም ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣውና

መመሪያ መሰረት እሰከ ብር 200,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች እንዲሁም እስከ ብር 150,000.00 የአገልግሎት ግዥ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ እንዲፈፀም ያዛል፡፡ ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ ሂሳብ ለማዘጋት የአቅም ውስንነት ስለገጠመን ለጊዜው ይህንን ችግር የሚፈታልን በኢፍሚስ ሙያ ያለው ባለሞያ እንዲያግዘን በማለት ያለምንም ውድድር እና መስፈርት ሰራተኛ በመቅጠራቸው በሂሳብ መደብ 2241101 (6251) ብር 56,200.00 አሳግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም

## ስጋት፤

- የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላል ፡፡
- የውስጥ ቁጥጥሩ የላላ ሊሆን ይችላል ፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ፤

አገልግሎት ግዥው ያለ ውድድር መከናወኑ የግዥ መመሪያ የጣሰ በመሆኑ ይህ አይነት አሰራር ሊቆምና ሊስተካከል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ይህንን የአገልግሎት ግዥ የፈቀደው ኃላፊ እና ክፍያውን የፈጸመው ሰራተኛ ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡

## የሥራ አመራሩ ምላሽ

ክፍያ የተፈጸመው ያለውድድር ለተቀጠረ ሠራተኛ አይደለም፡፡ ተቋሙ ቀደም ብሎ ይጠቀምበት የነበረው ከመንግሥት የፋይናንስ ምንጭ ውጪ ስለነበርና በኋላም ተቋሙ ወደ መንግሥት መደበኛ ትሬዠሪ ገንዘብ መጠቀም ሲጀምር ሂሳብ ሪፖርቱ በIFMIS ሲስተም ኢንዲደረግ ሲወሰን በወቅቱ የነበሩ 2 የሂሳብ ባለሙያ የነበሩና እነዚህም በቂ በIFMIS እውቀት ያልነበራቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተቋሙ ለበርካታ ወራት ያልተዘጋ ውዝፍ የሂሳብ ሪፖርት ተቋሙ ገጥሞታል፡፡ ስለሆነም ከገንዘብ ሚኒስቴር ተደጋጋሚ የሙያ እገዛ ብንጠይቅም ወቅቱም ኮቪድ 19 በአገራችን የተስፋፋበት ጊዜ ስለነበር አልፎ አልፎ ከገንዘብ ሚኒስቴር የሙያ እገዛ ለማድረግ የመጡት ባለሙያወችም በቂ እገዛ ማድረግ ስላለተቻለ የተቋሙ አካውንታንቶች ሙሉ ሂሳብ ሪፖርት ለመስራት ያልበቁ ስለነበርና ውዝፍ ሂሳቡ ባለመዘጋቱ ገንዘብ ሚኒስቴር ለስራ ማስኬጃና ለሌሎች ወጪዎች ገንዘብ ባለመልቀቁ ተቋሙ መፍትሄ ያለውን በባለሙያዎች ችግሩ ተጠንቶ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ በማቅረብ ውዝፍ ሂሳብ የሚሰራ የሙያ አበል የሚከፈለው ድርጅት በስምምነትና

በድርድር ሂሳቡንም ባለሙያዎችን እያሰለጠነ ሂሳቡ እንዲዘጋ የተደረገ ሲሆን ከዛ በኋላ ባለሙያዎችም ብቁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

ኢፍሚስ በተመለከተ ባለቤትነት ያለው ገንዘብ ሚኒስቴር በመሆኑ በመነጋገር ችግሩን መፍታት ሲገባ ባለሙያ እንዲያግዘን በሚል አላግባብ የኮንትራት ቅጥር መከናወኑ በተጨማሪም ቅጥሩም ያለውድድር መከናወኑ ተገቢነት የለውም፡፡ በመሆኑም አሰራሩ ሊታረም ይገባል፡፡

## 1.3 ግኝት፤ አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለተፈፀመ ግዥ የተከፈለ ብር 6,459,393.60

የፌዴራል መንግሥት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ መመሪያን የተከተለ ግዥ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የሰራተኛና እና የኃላፊ ወንበሮችን በቀን 27/09/13 ኢንቮይስ ቁጥር 1249 በሂሳብ መደብ 2311101 ብር 6,459,393.60 አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ ለተፈፀመ ግዥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**ስጋት፤**

ግዥዎች በወጣው መመሪያ መሠረት ባለመከናወናቸው መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ግዥዎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት ከነበረበት ቢሮ በአስገዳጅነት ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያለ ምንም ማሥጠንቀቂያ ለመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት ግንባታ በሚል በፖሊስ

ሁሉም ንብረቶች ወጥተው በኤርትራ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲጣሉ በመደረጉና ወቅቱም ክረምት በመሆኑ ያሉት የቢሮ መገልገያ እቃዎች በሙሉ በመውደማቸው፤

- ኢንስቲትዩቱን ለማጠናከር በተወሰደው እርምጃ በርካታ ተመራማሪዎችና ሰራተኞች በአንድ ጊዜ በመቀጠራቸው፤
- ተቋማችንአዲስ ቢሮ ተፈቅዶለት ወደ ስራ ሲገባ ምንም አይነት የቢሮ መገልገያ እቃ የሌለው በመሆኑ ምክንያት ምርጫችን ያለ ስራ መቀመጥ ወይም ቀጥታ ግዥ በመጠቀም ተጠያቂነት፤ግልጸኝነጽ ና ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ ለማኔጅመንት ኮሚቴ ቀርቦ በቃለ ጉባኤ ተይዞ የተወሰነ ሲሆን ተቋሙ መስራው ውጠየታማ እንዲሆንና ሰራተኞች በስራ ገበታቸው ተገኝተው እንዲሰሩ ግዥውም ጥራትና የመንግስት ሃብት እንዳይባክን በጥንቃቄ የተፈጸመ ነው። ከዚህም ህግና ስርዓትን በጠበቀ መልኩ የተፈጸመ ነው ስለሆነም ተቋማት ሀብት ንብረታቸው በተለያ መልኩ ሲወድም ወይም ጥቃት ሲደርስበት እንደ አስፈላጊነቱ በቀጥታ ግዥ እንደሚችሉ በመንግስት የግዥ አዋጅ አንቀጽ 51/ሐ መሰረት የተፈጸመ ሲሆን ይህ ባይሆን ግን በተቋሙ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችል ነበር

ስለሆነም ካለው አስገዳጅነት የተነሳ የተወሰደ መፍትሄ ስለሆነ መሆኑን ገልጸዋል።

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

ተቋማችን አዲስ ቢሮ ተፈቅዶለት ወደ ስራ ሲገባ ምንም አይነት የቢሮ መገልገያ እቃ የሌለው ለሚለው መ/ቤቱ የቆየና የነበረ በመሆኑ ባለው ንብረት እየተጠቀመ መመሪያን ተከትሎ ወይም የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ግዥውን መፈጸም ሲገባው ያለምንም ውድድር ግዥ መፈጸሙ ተገቢነት የለውም፤ በመሆኑ መመሪያን ያልተከተሉ ግዥዎች በመከናወናቸው የሚመለከተው አካል ተጠያቂ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ግዥዎች መመሪያን ተከትሎ እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 1.4 ግኝት፡- <u>ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ የደመወዝ ክፍያ ብር 942,779.60፤</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል2 ተራ ቁጥር 10 የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ አከፋፈል ፤የመንግስት ሰራተኞችን ደሞዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት ሊወስዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ ተ/ቁ 1 የስራ መደቡ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ያለው መሆን

እንዳለበት ይገልጻል ፡፡ይሁን እንጅ ለኢንስቲትዮቱ ሠራተኞች የመንግስት ተሻሚዎችን ሳይጨምር ከሀምሌ 1/2012 እስከ ህዳር 30/2013 የከፈለው ደመወዝ ብር 652,118.93 የደመወዝ እስኬሉና የስራ መደቡ ባለመታወቁ እንዲሁም የተለያዩ የአበል አይነት / የቤት አበል የትራንስፖርት አበል የልጅ ት/ቤት አበል../ ብር 290,660.67 አበሉ የተፈቀደበት ባለመቅረቡ በድምሩ ብር 942,779.60 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ የደመወዝ ወጪ መገኘቱ፡፡

*__ስጋት__*

*የመንግስት ደንብና መመሪያ የጣስ ሊሆን ይችላል፡፡*

*__የማሻሻያ ሀሳብ፤__*

*በክፍያ መመሪያው መሠረት የደመወዝ ክፍያው ከመፈጸሙ በፊትየስራ መደቡ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ያለው መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡*

*__የሥራ አመራሩ ምላሽ__*

*ተቋሙ በመንግስት በጀት ከመተዳደሩ በፊት የመንግስትን ህግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ የሰራተኞችን ቅጥር የማያካሂድ የደሞዝና ጥቅማጥቅም ክፍያዎችን ስርዓት ያልተከተሉ እንደነበር ሪፎርም ስንሰራ ወይም መልሰን ስናደራጅ እኛም ያረጋገጥነው ነው፡፡*
*ይሁን እንጅ መ/ቤቱ ለበርካታ አመታት እያገለገሉ የቆዩ ባለሙያዎችና ሰራተኞች ወደ ሪፎርም ስርዓቱ ለማስገባት በሚደረግ የሽግግር ወቅት ሲያገኙት የነበረውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም በአንድ ጊዜ ማቆምና ማሰናበት በሞራንም ይሁን በህግ ተጠያቂነት ከማስከተሉም በላይ ማህበራዊ ቀውስ የሚያመጣ ስለሆነ የህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተፈጸመ ሲሆን በእንዝላልነት ወይም በግዴለሽነት የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን ለማድረግ የታሰበ አይደለም፡፡ የአንድ ተቋም ሃላፊነት ነገሮችን ዙሪያ መለስ መመልከት እንጂ አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ የሚፈጸም ሊሆን አይገባውም፡፡ ጉዳዩ ለበርካታ አመታት ተከማችቶ የቆየ ከመሆኑ አንጻር መልክ ለማስያዝ ጊዜና አሰራር በመጠየቁ የገጠመ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡*

*__የኦዲተር አስተያየት__*

*ኢንስቲትዩቱ የመንግሥት መቤት እንደመሆኑ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ያለው የሥራ መደብ ባለው መዋቅር መሰረት*

የሠራተኞችን ደመወዝና ጥቅማጥቅም መክፈል ሲገባው በሥራ አመራር በተሰጠው ምላሽ መ/ቤቱ ለበርካታ አመታት እያገለገሉ የቆዩ ባለሙያዎችና ሰራተኞች ወደ ሪፎርም ስርዓቱ ለማስገባት በሚደረግ የሽግግር ወቅት ሲያገኙት የነበረውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም በአንድ ጊዜ ማቆምና ማሰናበት በሞራልም ይሁን በህግ ተጠያቂነት ከማስከተሉም በላይ ማህበራዊ ቀውስ የሚያመጣ ስለሆነ የህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተፈጸመ ነው የሚለው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደና የመደብ መታወቂያ ቁጥር ያለው የሥራ መደብ ባልቀረበበት የተከፈለው ደመወዝ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም ለተፈጸመው ክፍያ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተፈቀደ የሥራ መደብ ስለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

## 1.5 ግኝት፤ <u>ያላግባብ የተደረገ የደሞዝ ጭማሪ ብር 53,760.00</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል2 ተራ ቁጥር 10 መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ አከፋፈል የመንግስት ሰራተኞችን ደሞዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ሊወስዱ ይገባል ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ ተ/ቁ 6 በመንግስት የሚሾሙና በዝውውር ለሚመደቡ ሰራተኞች ይህንን አስመልክቶ የተሰጠ ትዕዛዝ መኖር እንዳለበት በቁጥር ሲሰኮ/ከቢ/214/2012 በቀን የካትት 20/2012/ዓ/ም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለኢንስቲትዩቱ የመንግስት ተሿሚዎች ደመወዝ ማስተካከያ ስለማሳወቅ በሚል በላከው ደብዳቤ ተ/ቁ1 የተቋም ዋና ዳይሬክተር ደመወዝ ብር 15,070.00 መሆንን ፤ ኮሚሽኑ ባጸደቀው መዋቅር/የስራ መደብ መጠሪያ ዋና ዳይሬክተርና ምክ /ዳይሬክተር ተሿሚ መሆናቸውንና ደረጃ የሌላቸወ መሆኑን አሳውቋል ፡፡ ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ ከላይ የተዘረዘሩት እያለ ከታህሳስ 1/2013 ጀምሮ ጂኤጂ ተግባራዊ በመሆኑ በሚል በሚመለከተው አካል ለቦታው የተፈቀደ ክፍያ መሆኑን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ሳይቀርብ ለኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ለአቶ ዮሀንስ ቢያለው የወር ደሞዛቸው 15,070 * 6 ብር 90,420.00 መክፈል ሲገባቸው ብር 21,468 *6=ብር 128,808.00 በመከፈሉ በልዩነት ብር 38,388.00 ፤ ም/ዋና ዳይሬክተር (አቶ በክር ሻሌ) 16,388*6= 98,328 መከፈል ሲገባው ብር 18,950.00 *6=113,700.00 በመከፈሉ ልዩነት ብር15,372.00 በጠቅላላ ድምር ብር 53,760.00 አለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡

## ስጋት

- የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላል፡፡
- የተመደበው በጀት ላልታለመለት አለማ ሊውል ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ፤

በሚመለከተው አካል ለቦታው የተፈቀደ ክፍያ መሆኑን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ማስረጃ መቅረብ የማይችል ከሆነ አላግባብ የተከፈለው የገንዘብ ልዩነት ተመላሽ ሊደረግ እና ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

## የሥራ አመራሩ ምላሽ

የዋና ዳይሬክተርና የም/ዋና ዳይሬክተርን የደመወዝ ጭማሪ ብር 53,760.00ተብሎ የተገለጸው በሚመለከት ኢንስቲትዩታችን የጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት እንደመሆኑ የራሱ የሆነ የደመዝ ክፍያ እና ጥቅማጥቅም እንዲኖረው በማስጠናት ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ሲያቀርብ መንግስት የምርምር ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ፣ተመራማሪዎችን በመንግስት መ/ቤት ውስጥ ለማቆየት የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓት ለማስያዝ እንዲቻል በማሰብ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሰኔ 16 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር መ50-8/3/3 በተፃፈ ደብዳቤ ለግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የተፈቀደ ጥቅማጥቅም እንድንጠቀም ሲፈቀድ ደመወዝን በሚመለከት JEG/ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን/ ተግባራዊ ከሆነ በኃላ የሚፈቀድ መሆኑን ተገልፃል፡፡ በመሆኑም በኢንስቲትዩቱ የሚደረጉ ምርምሮችና ውጤታቸወውን በሚመለከት ምርምሩን በበላይነት የሚመሩት እነዚሁ የሥራ ኃላፊዎች በመሆናቸው በኢንስቲትዩታችን መዋቅር በመስራት ስራዎቻችንን በJEG/ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን/ በማስመዘን ከታህሳስ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ በመሆኑ ለስራ ኃላፊዎችም የተደረገው የደመወዝ ማስተካከያ በቀድሞ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ጥቅማጥቅምን በሚመለከት ሲፈቅድ ደመወዛቸውን ግን በJEG/ ተግባራዊ ከሆነ በኃላ የሚታይ ይሆናል በሚል የተፈቀደ በመሆኑ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለዋና ዳይሬክተር እና ለም/ዋና ዳይሬክተር ተፈቅዶ የሚከፈል የደመወዝ መነሻ መሰረት በማድረግ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ የደመወዝ ማስተካከያው ተደርጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም የጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ተመሳሳይ ተቋማትና የዩኒቨርሲቲ ተሿሚዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ የኢንስቲትዩቱ ዳይሬክተሮች አስተዳደር ስራ ብቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ የምርምር ጥናት ስልጠናና መደበኛ የአመራር ስርዓትን አጠቃለው የሚሰሩ በመሆናቸው ደሞዛቸውና ጥቅማጥቅማቸው እንደማንኛውም ተሿሚ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

የኢንስቲትዩቱ ዳይሬክተሮች አስተዳደር ስራ ብቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ የምርምር ጥናት ስልጠናና መደበኛ የአመራር ስርዓትን አጠቃለው የሚሰሩ በመሆናቸው ደሞዛቸውና ጥቅማጥቅማቸው እንደማንኛውም ተሿሚ ተደርጎ አይወሰድም፡፡ለሚለው የሥራ አመራሩ ምላሽተገቢው የሰነድ ማስረጃ ሊቀረብ ይገባል፡፡

**1.6 ግኝት፤ ያለ አግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያን ብር 20,257.01**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/1/54/2/ በቀን 17/09/2002 ስለ ትርፍ ሰዓት ክፍያ አፈጻጸም በማስመልከት ከኤጀንሲዉ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 የተላለፈዉ የአፈጻጸም መመሪያ ተግባራዊ ሳይደረግ እንደቆየ ይታወቃል፡፡ መመሪያዉ በተለይም በሥራ ባህሪያቸዉ ምክንያት ከመደበኛ ሥራ ሰዓት ውጪም ጭምር ለሚሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች ጠቃሚ እንደሚሆን ስለታመነበት ያለአግባብ ብክነት እናዳይከሰት የተጠቃሚ መ/ቤቶች የሥራ ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ በማስገባት በኤጀንሲዉ በኩል በልዩ ሁኔታ እየተፈቀደ ሥራ ላይ እንዲዉል እንዲደረግ እናሳስባለን የሚል የተላለፈ ሲሆን በዚህ መልኩ ከሚኒስተር መ/ቤቱ እየተፈቀደ ብቻ የትርፍ ሠዓት እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በናሙናችን መሰረት ኢንስቲትዩቱ የሚመለከተውን መ/ቤት ሳያስፈቅድ አላግባብ በድምሩ ብር 20,257.01 ወጪ በማድረግ ለተለያዩ ሰራተኛች የትርፍ ሰዓት ክፍያ የፈፀመ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

**ስጋት፣**

- የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ዉጭ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ የሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ሲፈቀድ እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ክፍያው የተፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሳይሆን በመንግሥት ሠራተኛ የቀን ውሎ አበል መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 3 አንቀጽ 5 መሠረት ሠራተኛው ለመንግሥት ሥራ ከመደበኛ ቦታውና ሰዓት ውጭ በሚሰራበት ሰዓት የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ የምሳ አበል ይከፍላል ይላል። ስለሆነም የተከፈለው ገንዘብ በኃላፊው ትዕዛዝ ለኮሚቴ ሥራ ከሥራ ሰዓት ውጭ ለተሰራበት የምሳ አበል እንጂ የትርፍ ሰዓት ክፍያ አይደለም ።

<u>**የኦዲተር አስተያየት**</u>

በኦዲት ወቅት ከቀረበው ሰነድ ቅዳሜ እና ከሥራ ሰዓት ውጪ በሰሩበት በሚል የተፈጸመ ክፍያ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለሆነም የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ክፍያው መፈጸም ይገባል።

## 1.7 <u>ግኝት፤ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የውሎ የአበል ክፍያ ብር 4,035.00</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቀን 24/12/05 በደብዳቤ ቁጥር ሲ.ሰ.ማ/ሚዴን/127/05 የተሿሚዎች የቀን ዉሎ አበል አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ለከፍተኛ ኃላፊዎች የላሊበላ የቀን የዉሎ አበል ብር 525.00 እንደሆነ ይገልፃል። እንዲሁም የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 2 አንቀጽ 5 የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል ተ/ቁ 1 የቀን ውሎ አበል ተመን የሚሰላው ከአንድ ቀን የውሎ አበል ክፍያ ውስጥ ለቁርስ 10% ፤ለምሳ 25% ፤ለራት 25%፤እና ለአልጋ 40% በመመደብ መሆኑን ይገልጻል ። ይሁን እንጅ

- የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ የሚካተቱ እንደሆነ መመሪያው እየገለጸ ለኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ላሊበላ ለሄዱበት በቀን ብር 525.00 መከፈል ሲገባው ለበላይ ኃላፊዎች በተፈቀደዉ የውሎ አበል ብር 690.00 ክፍያ በመፈፀሙ እንዲሁም አልጋ በደረሰኝ ተወራርዶ እያለ 40% መቀነስ ሲገባው ባለመቀነሱ በአጠቃላይ ብር 4,035 አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ዝርዝር **በአባሪ 4** ቀርቧል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለሰልጣኞች የመመለሻ ቀን የምሳ ፤የአልጋና እራት 90% ቀንሶ መክፍል ሲገባው ሙሉ አበል /100%/ በመክፈል ብር 26,656.20 ያለአግባብ ወጪ መሆኑ፤እንዲሁም ስልጠናውን በስራ አመራር ኢንስቲትዩት የሚሰጥና ወጭው በመ/ቤቱ

የሚሸፈን ሆኖ ሳለ ለሰልጣኞች አበል በሚል በቀን 30/10/13 ኢንቮይስ ቁጥር 1639 ለቀን ብር 200.00 ለ16 ሰልጣኞች የ8ቀን ብር 25,600.00 በድምሩ ብር 52,256.20 ያለአግባብ ወጪ ሆኖ ተከፍሎ ተገኝቷል ፡፡ ዝርዝር **በአባሪ 8** ቀርቧል፡

**<u>ስጋት፤</u>**

ከደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>**

መ/ቤቱ አሁን ራሱን ችሎ በ2012 ዓ.ም በአዋጅ የተቋቋመ የመንግሥት መ/ቤት እንደመሆኑ ፡፡ በመሆኑም በመንግሥት ሠራተኞች የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሠረት የውሎ አበል ክፍያ ሊፈጸም ይገባል፡፡ አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ዉጭ የተከፈለ የአበል ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>**

የተጠቀሰው ግኝት ተመራማሪዎች ለስልጠን በሚሔዱበት ጊዜ የስልጠናው ወጭ በተቋሙ የሚሸፈን ከሆነ ለተለያዩ ወጭዎች የሚሆን በቀን ብር 200.00 እንደሚከፈል በተቋማችን ተግባራዊ እንዲሆን በጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት የተፈቀደው የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት መመሪያ ስለሚፈቅድ ይህን መመሪያ እንዲተገበር በተፈቀደው መሰረት የተፈፀመ መሆኑ፤

ከ3/10/2013 ዓ.ም እስከ 10/10/2013 ዓ.ም በደ/ዘይት ከተማ ለባለሙያዎች ይከፈል ከነበረው የመመለሻ ቀን አበል የምሳ ዕራትና አልጋ ያለ አግባብ ተከፍላል የሚል ሲሆን በትክክል ሰነዱን ለማየት የተሞከረ ሲሆን ተከፈለ የተባለው ገንዘብ ግን ክፍያ አልተፈጸመም ይልቁንም ለሰልጣኞች የቁርስ 10 መከፈል ሲገባው አልተከፈላቸውም፡፡ ስልጠናው ከ 3-10/10/2013 ዓ.ም የነበረ ሲሆን በነዚህ ቀናቶች 8 ስልጠና ቀኖች ያሉ ሲሆን መመለሻውን ቀን ሳይጨምር ክፍያ የተፈጸመው ግን የ7 ቀን ብቻ በመሆኑ ምንም አይነት ስህተት የለውም፡፡(አባሪ 6

**<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>**

በኦዲት ወቅት ከቀረበው ሰነድ 90% የቀን ውሎ አበል ለመቀነሱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም አለ አግባብ የተከፈለው ውሎ አበል ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ለወደፊቱም የአበል ክፍያን በተመለከተ በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

## 1.8 ግኝት፤<u>የተሟላ ማስረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 67,268.80</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 3 አንቀጽ 9 የቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅጾች ከቁጥር 1-4 ከመደበኛ የስራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ ስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ ፤መክፈያነና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሰራተኛ እንዲሞሉ ያዛል ። ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የሚፈፀሙ የአበል ወጪዎች በመመሪያው መሰረት የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥሮች ለአበል የተከፈለ ብር 67,268.80 መነሻና መመለሻ ቀን ፤ሰዓት ፤ቅጽ1 ፤የሚሄዱበት የስራ መዘርዝር ባለመሟላቱ የወጪን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል።

**<u>ስጋት</u>**

- የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላል።
- ክፍያው ለታለመለት አላማ ላይዉል ይችላል።
- የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም።

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>**

መ/ቤቱ የመንግሥት መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም በመመሪያው አስፈላጊውን የውሎ አበል ፎማርማሊቲዎች መሟላታቸው ሊረጋጥ ይገባል። ለወደፊቱም መ/ቤቱ በመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ሊፈጸም እንደሚገባ እናሳስባለን።

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>**

ወጪው ለመንግሥት ሥራ ጉዳይ የወጣ ሲሆን አበል ፎርሙ በትክክል የቁርስ፤የምሳ የራትና የአልጋ በማለት ተለያይቶ ያለተቀመጠ ቢሆንም ጥቅል ድምሩ ግን ትክክል ነው ሆኖም የተሟላ ሆኖ አለመሰራቱ ግን ሂሳቡን ከሚያዘጋጀው የሂሳብ ባለሙያ የሙያ ክፍተት በመኖሩ የተከሰተ ነው።

## 1.9 ግኝት ፤ ያለአግባብ ለሹፌሮች የተከፈለ አበል ብር 9,229.30

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የሾፌሮች መደቦች ላይ ተመድበው ለሚሠሩ ሠራተኞች ልዩ አበል ስለመፍቀድ ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም በፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ፐ/ስ/ስ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ/13/46/1010 በተጻፈ ደብዳቤ ከጥር 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከክፍያው ላይ ግብር እንዲቀነስ ሆኖ ለሾፌሮች አበል፡- በመንግስት ለተሾሙ የበላይ ሃላፊዎች በዘላቂነት አገልግሎት የሚሰጡ ሾፌሮች በወር ብር 800.00 ለከፍተኛ አመራሮች ቤተሰቦች፤ ለስራ ኃላፊዎችና በመደበኛነት የሰርቪስ አገልግሎት ለሚሰጡ የሰርቪስ ሾፌሮች በወር ብር 600.00 እንዲከፈላቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ከመመርያ ዉጭ የሰርቪስ አገልግሎት ለሰጡ ሾፊሮች በሂሳብ መደብ 6231 የእራት እና የቁርስ አበል ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 9,229.30 አላግባብ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**ስጋት**

- የመመሪያ ጥሰቶችን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላሉ፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመው ክፍያ ሊቆም ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የሾፌሮች አበል ክፍያ የተፈጸመው በፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ኃብት ሚኒስቴር በቁጥር ፐ/ስ/ስ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ/13/46/10/0 ከጥር 01 ቀን 2008 ዓ.ም. በተጻፈው በበላይ ኃላፊዎች አገልግሎት ለሚሰጡ ብር 800.00 ለከፍተኛ አመራር ቤተሰቦች ለሥራ ኃላፊዎች ለሚሰጡ ደግሞ ብር 600.00 በተፈቀደው ደብዳቤ መሠረት የተከፈለ ሳይሆን የተወሰኑ የተቋማችን ሠራተኞች የመኖሪያ አድራሻ ከሥራ ቦታ ክልል ውጭ ማለትም ሰበታ ከተማ ስለሚኖሩ ለዳይሬክተሮቹ ጠዋት እና ማታ የሰርቪስ አገልግሎት በተሰጠበት ወቅት የተከፈላቸው መደበኛ የአበል ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት የተከፈለ ሲሆን የሰርቪስ አገልግሎት የተሰተጠበት ምክንያት በወቅቱ በአገራችን የኮሮና ቫይረስ የተስፋፋበትና ሥርጭቱ

የጨመረበት ጊዜ ስለነበር ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለ2 የሥራ ክፍል ኃላፊዎች (ዳይሬክተሮች) ተብሎ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በኃላፊ ተፈቅዶ የተፈጸመ ነው፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

በሥራ አመራር ምላሽ መሠረት ክፍያው የተፈጸመው የተቋሙ ሠራተኞች የመኖሪያ አድራሻ ከሥራ ቦታ ክልል ውጭ ማለትም ሰበታ ከተማ ስለሚኖሩ ለዳይሬክተሮቹ ጠዋት እና ማታ የሰርቪስ አገልግሎት በተሰጠበት ወቅት የተከፈላቸው መደበኛ የአበል ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት የተከፈለ ሲሆን የሰርቪስ አገልግሎት የተሰተጠበት ለሚለው የመ/ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊዎች (ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ) በስተቀር ለተጠቀሱት ሰራተኞች መንግሥት የመደበው ፐብሊከ ሰርቪሰ አለ መጠቀም ሲገባ አለ አግባብ ክፍያ ሊፈጸም አይገባም፡፡ በሌላ መለኩ መኪና የተፈቀደላቸው ዳይሬክተሮች በራሳቸው ማሽከርከር ከቻሉ ራሳቸው እንዲዙ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ክፍያው እንዲቆም እና በፐብሊክ ሰርቪሰ መኪና ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

## 1.10 <u>ግኝት፤ በመመሪያው መሰረትያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ ብር 3,889.03</u>

ህዳር 1999 የወጣው የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነፃ ህክምና መመሪያ ቁ.5 መሰረት የአገር ውስጥና የወጭ አገር ህክምን እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የመንግስት ሀላፊዎች ከደመወዛቸው 2 % እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ሀላፍዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል አለባቸው ይላል ፡፡ ይሁን እንጅ ኢንስቲትዩቱ በመመሪያው መሰረት ባለመቀነሱ ብር 3,889.03 ሳይሰበሰብ እንደቀረ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

**<u>ስጋት</u>**

የመንግሥት መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ኢንስቲዩቱ የመንግሥት መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን መንግሥት የሚያወጣው መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ያልተቀነሰውን የህክምና መዋጮ ተቀናሽ ሊደረግና ለሚመለከተው አካል ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

ሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል።

## 1.11 <u>ግኝት፤ያለአግባብ የተከፈለ ጥቅማ ጥቅም ብር 1,152,466.00</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 6/1 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኘው የመንግስት ሃብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው ይላል፤ይሁን እንጅ መ/ቤቱ በአዋጅ የተቋቋመ መ/ቤት ሆኖ ሳለ ጥቅማጥቅም በሚመለከተው አካል አስፈቅዶ መጠቀም ሲገባው ያለምንም ፈቃድ ለተመራማሪዎች ጥቅማጥቅም በሚል ከታህሳስ 1/2013 እስከ ሰኔ 30/2013 ብር 1,152,466.00 ያለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡

**<u>ስጋት</u>**

የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል።

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

መ/ቤቱ አሁን ራሱን ችሎ በአዋጅ የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን የራሱን ጥቅማ ጥቅም አስፈቅዶ መጠቀም ሲገባው በ2010 ዓ/ም የተፈቀደለትን የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጥቅማጥቅም ተግባራዊ ማድረጉ እንዲሁም የግብርና ምርምሩ በሚመለከተው አካል አስፈቅዶ የጥቅማጥቅም ጭማሬ ሲያደርግ ተመርማሪ መ/ቤቱም በድጋሜ ሳያስፈቅድ የጥቅማጥቅም ለውጥ ማድረጉ አግባብነት የለውም። በመሆኑም አላግባብ የተከፈለው ጥቅማ ጥቅም ሊቆምና ሊፈቀድ ይገባል ፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

በየደረጃው ላሉ ተመራማሪዎች የቤት አበልንና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በሚመለከት የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ ቤት ሰኔ 16 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር መ50-8/3/3 በተፃፈ ደብዳቤ ከዋና ዳይሬክተር ጀምሮ እስከ ጀማሪ ተመራማሪ ሥራ ላይ ላሉ ኃላፊዎችና ተመራማሪዎች የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን የተፈቀደ ጥቅማጥቅም እንዲከፈል በፈቀደው መሰረት ከጥቅማጥቅሞቹ አንዱ የቤት አበል በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ተደረገ ክፍያ ነው ስለሆነም ይህንን በግኝት መያዝ የለበትም፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

መ/ቤቱ እደገና በአዋጅ በመቋቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የራሱን ጥቅማ ጥቅም በሚመለከተው አካል ሊያስፈቅድ ይገባል፡፡

## 1.12 ግኝት፤በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ሂሳብ ብር 30,077.00

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በተለያየ ቀንና የኢንቮይስ ቁጥር በድምሩ ብር 30,077.00 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝተዋል፡፡

**ስጋት፤**

የሚወጡት የሂሳብ ሪፖርቶችን ትክክኛ ገጽታ አይሳይም ፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ሂሳቦች በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ተመዝግበው በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ተቋማችን ይጠቀምበት ከነበረው መስቀል አደባባይ ከሚገኘው ቢሮው ወደ ስታዲየም ጊዮን ሆቴል ጎን ቢሮ ሲቀይር በቀን ሰራተኛ የሚመላለሱ ቦሮ እቃዎች እንዲሁም ለቢሮ ጽዳት ማስተካከል የተተከፈሉ ቀን ሰራተኛ ክፍያዎች በቀን ሰራተኛ ለሚከፈሉ በሚል የሂሳብ ኮድ ገንዘብ ስለሌለ ተመሳሳይነት አለው በሚል እሳቤና ያለው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት አነስተኛ ነው

በሚል አገልግሎት ክፍያዎች በሚፈጸምበት ኮድ  ክፍያ ተፈጽል ስለሆነም ወደፊት የሚስተካከል ሆኖ እንደ ግኝት ግን የሚያዝ አይደለም፡፡

2 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

2.1 ግኝት፤ <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር157,687.48</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኂላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ የባለስልጣኑ የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 157,687.48  ለተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች  ቅድመ ክፍያ የተከፈለ እና ከ1ወር በላይ የቆየ እና ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበ ትህዳር 30/2014 የቆየ እና በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ ተይዞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ ሊያደርግና ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ቅድመ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲወራረዱሊወራረድ የማይችለው ከሚመለከታቸው ድርጅቶችም ሆነ ሰራተኞች ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 3 ተከፋይ ሂሳብ፤

### 3.1ግኝት፤ ለባለመብቱ በወቅቱ ያልተከፈለ፤ ብር679,868.23

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር5/2003 ክፍል አንድ ላይ ተከፋይ ሂሳብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ሂሳብ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ ወይም የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ 6172110 ገቢታ ለሀገረ በሚል ብር 45,034.40 የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት (ለኮስት ሼሪነግ) ብር 15,200.00 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6174208 ለገቢዎች ተከፋይ በሚል ብር619,633.9 በድምሩ 679,868.23 ብር በወቅቱ ለባለ መብቱ ያልተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦል፡፡

**በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፤**

የተከፋይ ሂሳብ መጠን ከፍ ብሎ የታየው በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ወርሃዊ የዊዝሆልዲንግና የቫት ተከፋይ በሰኔ 27 ቀን ከተከፈለ በኋላ ሰኔ 30 ላይ የተደረገ የአይቲ መሰረት ልማት ዝርጋታ ቅድመ ክፍያ ላይ የተቀነሰ 619,633.87 ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ለገቢዎች ባለስልጣን ተከፍሏል፤ ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ በወቅቱ ያስተላለፈበት ምክንያት የባለመብቶች ትክክለኛ አድራሻ እና የባንክ ቁጥር ባለመገኘቱ ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩት ተከፋይ ሂሳቦች በ2014 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ክፍያ ተፈጸሚል፡፡

**ስጋት፤**

- በተከፋይ የሚያዙ ሂሳቦች ላይከፈሉ ይችላሉ፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

በኦዲት ወቅት በተሰጠው ምላሽ ለገቢዎች ባለስልጣን ተከፍሏል ቢባልም ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ክፍያ የተፈጸመባቸው ተከፋይ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡ እንዲሁም መከፈል የሚገባቸውና ያልተከፈሉ ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቶቹ በወቅቱ እንዲከፈሉ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ምላሽ አልተሰጠም፡፡

4 **<u>በጀት፤</u>**

**<u>4.1 ግኝት ፤ ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 20,037,143.45</u>**

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ለመደበኛ በጀት ከተደለደለው በበጀት ዓመቱ ለመደበኛ ወጪዎች ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ያለው ለየሂሳብ መደቦቹ ከተፈቀደው ብር ውስጥ 49,236,027.65 **ብር 20,037,143.45** (40%) ስራ ላይ ያልዋለ ሲሆን ከአጠቃላይ በጀት ደግሞ ሲታይ ደግሞ 39.13% መሆኑ ታውቋል ፡፡ዝርዝር በአባሪ 13 ቀርቧል፡፡

**<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፤</u>**

የተጠቀሰው በጀት ስራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት ተቋሙን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በ2013 በጀት ዓመት 3ኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ 38 ሚሊዮን ብር በተጨማሪ በጀት የተፈቀደ ሲሆን የጨረታ ሂደቶች በመንተታቸውና የመንግስት የማዕቀፍ ግዥ ከአቅራቢዎች የተሰጡ የግዥ ትዕዛዞችን ማቅረብ ስላልቻሉ የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ እንዳናውል ምክንያት ፈጥሯል፡፡

**<u>ስጋት</u>**

በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የኢኒስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>**

በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የተጠቀሰው በጀት ስራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት ተቋሙን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በ2013 በጀት ዓመት 3ኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ 38 ሚሊዮን ብር በተጨማሪ በጀት የተፈቀደ ሲሆን የጨረታ ሂደቶች በመጓተታቸውና የመንግስት የማፅቀፍ ግዥ ከአቅራቢዎች የተሰጡ የግዥ ትዕዛዞችን ማቅረብ ስላልቻሉ የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ እንዳናውል ምክንያት ሆኗል።

## 5 ንብረት፤

### 5.1ግኝት፤ የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ ፤

የኤጀንሲውን የንብረት አስተዳደር በፌዴራል መንግሥት የግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 8 ፊደል ተራ /ሽ/ድንጋጌ መሰረት በመ/ቤታቸው ስር የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ የመንግስት ንብረቶች በህጉ በተፈቀደው የማስወገጃ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በወቅቱ እንዲወገዱ የተደነገገ ሲሆን የንብረት አያያዝና አወጋገድ በዚህ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ ንብረት አያያያና አጠባበቅ በዓዋጁ መረት መሰረት ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤-

- አስቸኳይ በሚል በቀጥታ ግዥ ከተገዙት የሰራተኛ ወንበሮች ውስጥ 31 በንብረት ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው ፤
- በንብረት ክፍል (እስቶር) ውስጥ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተዉ ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው ያልተጠበቁ መሆኑ፤
- የሚወገዱ ፤ወንበሮች፤ጠረጴዛዎች የተለያዩ ዕቃዎች መወገድ ሲኖርባቸዉ ያልተወገዱ በንብረት ክፍልና ከንብረት ክፍል ወጭ የተከማቹ ሆነው ተገኝቷል፡፡

**ስጋት፤**

- የንብረት አስተዳደር ቁጥጥሩ የላላ ሊሆን ይችላል፡፡
- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው የመንግሥትገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>**

ንብረቶች አገልግሎት የሚሰጡት አገልግሎት ከማይሰጠው ተለይቶ ሊቀመጥ እንደሚገባና፤ ሊጠገኑ የሚችሉት ተጠግነው አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ በአጠቃላይ መ/ቤቱ በመንግሥት ንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅ እና አመዘጋገብ መመሪያ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

የተገዙት ወንበሮች 110_/አንድ መቶ አስር/ ሲሆኑ 79 ወንበሮች ለሠራተኞች ስከፋፈል 31 ወንበሮች ለስልጠና የዳይሬክቶሬት(ቅጥር ያልተፈጸመለት ዳይሬክቶሬት) እና አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች ለመከፋፈል በንብረት ክፍል የተቀመጠ መሆኑን፤

የሚወገዱ ንብረቶች በተመለከተ በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ዋጋ ገማች እና ንብረት ማስወገድ ኮሚቴ በደብዳቤ ተቋቋሞ እየሠሩ የቆዩ እና በአሁኑ ሰዓት በግልፅ ጨረታ ወቶ ንብረቶቹን ለማስወገድ ሂደት ላይ የሚገኝን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

በአስቸኳይ ግዥ የሚፈጸምባቸው ዕቀዎች በክምችት ለጉዳት ሳይዳረጉ ለታቀደለት ዓለማ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

**በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገው የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡**